

# ግንቦት 7 Ginbot 7

## የፍትሕ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

## Movement for Justice Freedom and Democracy




ውድ ወገኖቼ

ሃገራችን ያለችበትን አሳዛኝና አደገኛ ሁኔታ ለእናንተ ለማስረዳት ብሞክር ድፍረት ይሆንብኛል። እናንተ ያልተገነዘባችሁት በሃገራችንና በወገናችን ላይ ያልተፈፀመ በደልና ግፍ የለም። እናንተ የማታውቁት አሳዛኝና አሳፋሪ የሃገራችን ገበናም አይገኝም። በመሆኑም ይህን ሰነድ ያዘጋጀንበት ምክንያት የምታውቁትን ለመድገም አይደለም። ግንቦት7 ምን ሲያደርግ እንደነበርና ምን እያደረገ እንደሆነ ለመግለጽ እንጅ።

በተደጋጋሚ ለምንሰማው "ለምን አንድ ነገር አታደርጉም?" ለሚለው ጥያቄያችሁ "ግንቦት 7" ምን እያደረገ እንደሆነ ከየት ተነስቶ የት ለመድረስ እንደሚፈልግ በእዚህ ሰነድ ውስጥ እንገልጻለን። ነገር ግን ለእዚህ ተገቢ ጥያቄያችሁ "እናንተስ ምን እያደረጋችሁ ነው?" ብዬ ብጠይቅ ከድፍረት እንደማትቆጥሩብኝ እተማመናለሁ። ለኢትዮጵያ ህልውና፣ አንድነት፣ ለህዝቧ ነጻነትና መብት፣ ለሰላምና ለብልጽግናዋ መታገል የኔና የጥቂት የትግል አጋሮቼ እዳና አደራ ነው ያለው ማነው? ሃገራችን የሁላችንም እናት አይደለችምን? የሚደማው የሚራበው የሚዋረደው የእኔም፣ የእርስዎም፣ የሌላውም ወገናችን አይደለምን? ብዬ እጠይቅዎታለሁ። የኢትየጵያ ጉዳይ ለጥቂት ነጻ አውጭዎችና የተለየ ተልእኮ አለን ለሚሉ ግለሰቦች መተው የለበትም የምለው ያለምክንያት አይደለም። ይህን የምለው፣ የኢትዮጵያን ጉዳይ ለጥቂቶች በመተው የመጣውን አስከፊ መዘዝ በማየቴ ነው፡፡ የሀገሩን ህልውና፣ ነጻነቱንና መብቱን ለማስከበር ያልታገለ ህዝብ፣ በቆራጦች ትግል ነፃነቱ እንኳ ቢሰጠው፣ ጠብቆ ሊያቆየው አይችልም የሚል ስጋት ስላለኝ ነው።

ያለንበት ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጣችሁ እንዳላችሁ አውቃለሁ። ተስፋ የምንቆርጠው ባስቀየሙን የፖለቲካ ሰዎች ላይ ይሆናል እንጂ በሃገራችን ላይ ሊሆን እንደማይችል እገምታለሁ። ማስታወስ ያለብን፤ "አባት የሞተ እንደሁ ባገር ይለቀሳል አገር የሞተ እለት ወዴት ይደረሳል" የሚለውን የእናቶቻችንን ለቅሶ ነው። አገዛዙ የተያያዘው ሃገር መግደል ነው። ኢትዮጵያዊ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ተስፋ የሚቆርጥ ዜጋ እንደሌለ አውቃለሁ። ለሃገራችን ጥፋትና ውድመት የሚመኙላት በሙሉ ማለፍ ያልቻሉት ፈተና ይህ በሁላችንም ልብ ውስጥ ቤቱን የሰራውን፣ ሁላችንም ለሃገራችን ያለን ፍቅር ነው።

የኢትዮጵያ ጉዳይ አማራጭ የሌለው እስከሆነ ድረስ እየወደቅን እየተነሳንም፣ ከጥፋታችን እየተማርን፣ የተለያዩ የትግል ስልቶችንና የድርጅት አማራጮችን እያፈላለግን ፣ የተከፈለውን መስዋእትነት ሁሉ ከፍለን ሃገራችንን እናስከብራለን ከማለት ሌላ አማራጭ የለንም። ይህን ከተረዳን፣ ለሀገራችን ህልውናና ለሁላችንም ደህንነት መጠበቅ፣ እያንዳንዳችን የድርሻችንን ማበርከት ይኖርብናል እላለሁ።

"የግንቦት 7 ንቅናቄ" በኢትዮጵያውያን የተባበረ ጥረት፣ የማይሸነፍ የሃገርና የወገን መከራና ጣዕር የለም የሚል እምነት አለው። ግንቦት 7 በእዚህ ሃገርን የማዳን ትግል ውስጥ፣ የንቅናቄውን መሪዎች ወይም አባላት ፍላጎት ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት በማስቀደም እንደሚሰራ፣ ለሃገራችን ቀና አመለካከት ካላቸው ወገኖች ጋር ተባብሮና ተደጋግፎ ለመንቀሳቀስ እንደሚጥር፣ ነገር ግን ሃገራችንና ሁላችንንም አዋርደው ለመግዛት ከሚፈልጉት ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ግን በቁርጠኛነት አምርሮ እንደሚታገል ቃል ገብቷል። እርስዎስ?

በእዚህ ሰነድ ውስጥ የሰፈሩትን ሃሳቦች በጥሞና ያንብቡ፣ ለትግሉ የድርሻዎትን ያበርክቱ፣ ግንቦት 7ን ይቀላቀሉ፣ ይደግፉ እላለሁ።

መልእክቴን ስላነበቡ አመሰግናለሁ

ብርሃኑ ነጋ

## ግንቦት 7 ፣ ወያኔ/ኢህአዴግን እንዴት ያየዋል?

- ወያኔ/ኢህአዴግ በጥቂት ጸረ- ኢትዮጵያ ሃይሎች ቁጥጥር ስር የሚገኝ ድርጅት ነው። በመሆኑም የሃገራችን ሉአላዊነትም ሆነ ብሄራዊ ጥቅሟንና ደህንነቷን እንደተራ ሸቀጥ ለመነገድ የማይመለስ መሆኑን በደርጊቱ ያረጋገጠ ድርጅት ነው።

- ወያኔ/ኢህአዴግ ዘረኛና አምባገነን ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሀገርንና የህዝብን አንድነት ለማፈራረስ ታጥቀው በተነሱ ጥቂት ግለሰቦች የሚዘወር ነው።

- ወያኔ/ኢህአዴግ ህልውናውን ለማስጠበቅ ዘረኛ በሆነ መንገድ ስልጣንና ጥቅምን እያካፈለ ህብረተሰቡን ለዘረኛ ስሜት መነሳሳትና መተላለቅ በማዘጋጀት ላይ ያለ ድርጅት ነው።

- ወያኔ/ኢህአዴግ ህግን እየፈነገጠ፣ የዜጎችን መብት እየገፈፈ «ግዜው የእኛ ነው» በሚል የዘመነ መሳፍንት ፍልስፍና፣ የሀገሪቱን ህዝብ በእብሪት አዋርዶ፣ የሃገሪቱን ሃብት በማንአለብኝነት እየዘረፈ ለመቀጠል ቆርጦ የተነሳ ድርጅት ነው።

- ወያኔ/ኢህአዴግ በምንም አይነት መንገድ አምባገነናዊ ስልጣናቸውንና ከእዚህ ስልጣን የመጣ ሃገር የመዝረፍ መብታቸውን፣ ለሀገርና ለወገን በሚሉ ታላቅ ራእዮች ስር ለማስገዛት የሚያስችል ሃገራዊ ፍቅር፣ ሰብአዊ ስሜትና አርቆ ማሰብ የሚያስችል እውቀት በሌላቸው "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል ብሂል በሚመሩ የትናንት ሰዎች ሙሉ ቁጥጥር ስር የወደቀ ድርጅት ነው።

## ወያኔ/ኢህአዴግ ሊቀየር ይችላል ወይ?

ግንቦት 7 ፣ ወያኔ/ኢህአዴግ የማይቀየር ድርጅት ነው ይላል።

የመሪዎቹ ጸረ ኢትዮጵያዊነት፣ ስር የሰደደ በመሆኑ አይቀየሩም።

- ልመናና ተማጽኖን እንደ ፍርሀት ወስደው፣ እንደማናቸውም አምባገነኖች፣ ለበለጠ እብሪት የሚዘጋጁ ገዥዎች ያለው ድርጅት ስለሆነ ወደ በጎ አቅጣጫ ፊቱን አያዞርም ።

- ቃል በመግባት፣ ለዘረፉችሁት የሀገር ሀብት፣ ለፈጸማችሁት ሃገራዊ ክህደትና ላጠፉችሁ የሰው ነፍስ በወንጀል አትጠየቁም ቢባሉም ከራሳቸው ቃል አባይነትና የክህደት ታሪክ በመነሳት ማንንም አምነው ለእርቅና ለድርድር የሚመጡ መሪዎች የሌሉት ድርጅት ነው። የወያኔ/ኢህአዴግ ገዥዎች የተጠናወታቸው አምባገነናዊ አባዜ የእርቅና የስምምነት ግብዣ የሚያቀርቡላቸውን በሙሉ በንቀት እንዲያዩ የሚያበረታታቸው እንጂ ቀና ልቦና እንዲገዙ የሚያደርጋቸው አይሆንም።

- የፈጸሙት ወንጀል ብዙ በመሆኑ ከሃገራቸው ህዝብ አልፎ አለም አቀፉ ህብረተሰብ በወንጀል ይጠይቀናል የሚል ስጋት ስላላቸው እስከ መጥፊያቸው ቀን ድረስ በስልጣን ለመቀጠል ቆርጠው የተነሱ ወንጀለኞች ናቸው።

- የሃገሪቱን ችግር በድርድርና በውይይት ለመፍታት ፈቃደኛ ሆነው አይመጡም። ምክንያቱም ድርድሩና ውይይቱ የሀገራችን ህዝብና የሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች መብቶች በእኩልነት ማስተናገድ ወደሚችሉ ተቋማት ምስረታ እንደሚያመራ ያውቃሉ። ነጻ ተቋማት ባሉበት የሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ጠቅልሎ ከስልጣናቸውና ከጥቅማቸው እንደሚነቅላቸው ከግንቦት7 1997 ምርጫ በቂ ትምህርት ስለወሰዱ ቢሞቱም ወደ ፍትሃዊ ምርጫ ወደሚወስድ ድርድር ውስጥ አይገቡም።

# ግንቦት 7 ፧ ወያኔ/ኢ.ህአዴግን ምን እናድርገው ይላል?

በቅድሚያ ወያኔ/ኢ.ህአዴግን ምን እናድርገው የሚለው ጥያቄ ምላሽ ወያኔ ኢ.ህአዴግ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ ከሰጠነው ምላሽ የሚመነጭ ነው።

- ወያኔ/ኢ.ህአዴግ ልመና፣ ተማጽኖ፣ እርቅ፣ ድርድር፣ ስምምነትና ሌሎችም ስልጡን የሆኑ የቅራኔ መፍቻ መንገዶች የማይገባው፣ ጸረ ኢ.ትዮጵያ ሃይል ነው ካልን፣ የሚኖረን ምርጫ አምርረን ታግለን ማስወገድ ብቻ ነው።
- አምርሮ ለመታገል፣ ዐይኑን አፍጦ የመጣውን እውነታ መቀበል ይኖርብናል። ጊዚያዊ የሆነውን የወያኔ/ኢ.ህአዴግ  ወታደራዊና የስለላ አቅሙን ፈርተን፣ በተቃዋሚው መከፋፈልና መዝረክረክ ተቆጭተን፣ ጠንካራ የሆነ የተደራጀ ሃይል ለማየት ባለመቻላችን ወያኔ ፈጽሞ መልበስ የማይችለውን የሰላምና የእርቅ ቀጤማ በማንጠፍ፣ ድንገት ለሰላምና ለህግ ተገዥ የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ወደሚል ቀቢጸ ተስፋ ማምራት አይኖርብንም።
- ለሃገራቸውና ለወገናቸው የሚቆረቆሩ ዜጎች በመሉ በወያኔ ማንነት ላይ ግልጽ የሆነ የጋራ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። በእዚህ ግንዛቤ ላይ በመቆም ብቻ ነው አሸናፊ ሆኖ መውጣት ስለሚገባው የትግል ስልትና ስትራተጂ ማሰብ የሚቻለው። ወያኔ/ኢ.ህአዴግ ከላይ ባስቀመጥናቸው ምክንያቶች በማያሻማ ቋንቋ ጠላት መሆኑን በማስቀመጥ፣ መስመር ሳያሰምር የሚጓዝ የፖለቲካ ድርጅት እራሱ በሚፈጥረው ብዥታ ራሱንም ደግፈኝ የሚለውን ህዝብ ማስመታቱ አይቀርም። የባላንጣን ምንነት አስቀድሞ ማወቅ ትግሉ የሚያስፈልገውን ግብአቶች ብዛት፣ ስፋትና ጥልቀት ለማወቅ ይጠቅማል። የትግሉን መራራነትና የሚጠይቀውን መስዋእትነት አስቀድሞ ለመረዳት ያግዛል። በግብር ይውጣ፣ በያዝ ለቀቅና፣ አየር ላይ በተመሰረተ ተስፋ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ከልብ እንድንቀበል ያደርገናል።

- በተቻለ መጠን ለሰላም፣ ለመረጋጋትና ለአንድነት ቅድሚያ በሚሰጥ የተባበረና በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ አነስተኛ ኪሳራ በሚያስከትል የትግል ስልትና ስትራተጂ ወያኔ ኢ.ህአዴግን ከሰልጣን ከመንቀል በስተቀር ሌላ አማራጭ የለንም። ለወያኔ/ኢ.ህአዴግ መልእክታችን ግልጽና የማያሻማ ሊሆን ይገባዋል። "በሃገራችን ሉአላዊነት፣ በአንድነታችን፣ በመብታችንና በሀገራችን ህዝብ ሃብት ላይ እንደራደርም። የአምባገነኖችን ለከት-የለሽ የጥፋት እርምጃ ፈርተን በባርነት አንኖርም። ሃገራችን እንድትበጣጠስ አንፈቅድም። አምርረን እንታገልሃለን። ትግላችን ፍትሃዊ ፣ በሚሊዮኖች የሚደገፍ ነው። በላቀ እውቀትና ሃገራዊ ራእይ የሚመራ በመሆኑ እናሸንፍሃለን፡፡ "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ...." ልንለው ይገባል።

- አምባገነኖች፣ በህዝባችን ሁለ-ገብ የትግል ስልት ከግራ ቀኝ ሲላጉ እና መግቢያ ቀዳዳ ሲያጡ ብቻ ራሳቸው ለምነው እንታረቅ የሚል ምልጃ የሚልኩ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል። እንዲህ አይነቱን አስገዳጅ ሁኔታ ፈጥረን የወያኔ/ኢ.ህአዴግ ገዥዎች መደበቅያ እንደማይኖራቸው አውቀው ልመና እስከሚመጡ ድረስ የስራ ድርሻቸው ሃገር ማጥፋት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ለእዚህም ነው አምርረን ለመታገልና ለማስወገድ መነሳት የሚኖርብን። በታክቲክ ደረጃ እንዲህ አይነቱ የለየለት አምባገነናዊና ፀረ ሃገር አገዛዝ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሃገራችን ለመፍጠር ለምንፈልገው የፖለቲካ ስርአት በጎ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚል ስሌት ከትግል እቅዳችን ማውጣት ይኖርብናል። ይህንን የተረዳ አካል ብቻ ነው፤ ትግሉን በሚገባ አቅዶ፣ የሚጠይቀውንም ግብአቶች  በማሟላት ለድል መብቃት የሚችለው።

# ወያኔ/ኢህአዴግን የማስወገዱ ሂደት፤ የመጀመሪያው ምእራፍ



ትብብር፣ የመተባበሪያ መርሆዎች፣ የትብብር ተግባራት

- ይህ ምእራፍ፣ የሃገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ሳይናጋ፣ ወያኔ የሚፎክርበትን እኔ ከሞትኩ ሃገሩን አፈርሰዋለሁ የሚለው ድንፋታ ማስቆም የሚያስችል ዝግጅት የማድረጊያ ምእራፍ ይሆናል።

- ግንቦት 7፣ ይህንን አደጋ መከላከል የሚቻለው በሃገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት በጋራ በመተባበር ወያኔ/ኢህአዴግ በዘርና በሃይማኖት ህዝብን ለማጫረስ ያሴረውን ደባ ለማክሸፍ በጋራ ተባብረው መስራት ሲችሉ ነው ብሎ ያምናል።

- ግንቦት 7፣ ይህ ትብብር መሰረታዊ በሆኑ የዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ የጋራ አቋም ባላቸው አካላት ይመሰረታል ብሎ ያምናል። እነዚህ መርሆዎች የሚከተሉት ይሆናሉ። ማንኛውም ዜጋ በህግ ፊት እኩል ነው። ማንኛውም ዜጋ አንድ ሰው አንድ ድምጽ በሚለው መርህ ላይ የቆመ እኩል የፖለቲካ መብት አለው። የመንግስት ስልጣን ከሃገር አቀፍ ደረጃ አንስቶ እስከ ዝቅተኛው የመንግስት አስተዳደር የሚወርደው ህዝብ በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮቹ ይያዛል። ማንኛውም ዜጋ የተሟሉ የሲቪልና የሰብአዊ መብቶቹ ሙሉ በሙሉ ይከበራሉ። ዜጎች የወል መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር በቡድን በነጻ የመደራጀት መብቶቻቸው ይከበራሉ የሚሉት ይሆናሉ።

- ግንቦት 7፣ ስለዜጎች መብት መከበርና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ስለሚመሰረት መንግስታዊ አስተዳደር በጋራ መምከር የሚቻለው፣ መብታቸው የሚከበርላቸው ዜጎች የሚኖሩበት፣ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቋቋመው መንግስት የሚመሰረትበት ሃገር የሚባል ነገር ሲኖር መሆኑን ያምናል። ግንቦት 7 ትብብር የሚፈጥረው ይህንን መሰረታዊ ነጥብ ተገንዝበው የኢትዮጵያን ልኡዋላዊ አንድነት ተቀብለው ግልፅና የጠራ አቋም ከያዙ አካለት ጋር ብቻ ሊሆን ይገባዋል ብሎ ያምናል።

- ግንቦት 7፣ ይህ ትብብር ከላይ በተጠቀሱት መርሆዎች ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎችን ያስተባብራል፡፡ ለህዝቡ አንድ አይነት የትግል ጥሪ ማድረግ፤ ይህን ትግል ወደ ዘረኛ የርስ በርስ ግጭትና ሌሎችንም ሰላምና መረጋጋት የሚያፋልሱ ድርጊቶች ለመቀየር በወያኔ/ኢህአዴግ የተቋጠረውን እኩይ ደባ ህዝብ በንቃትና በተደራጀ መልኩ ለማክሸፍ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤ የአመጽ ሃይሎች በተናጠል በመንቀሳቀሳቸው ሊያመጡ የሚችሉትን አደጋ በመረዳት በአንድ የተጠቃለለ እዝ ስር የሚገቡበትን ሁኔታ ባስቸኳይ መፍጠር፤ በዲፕሎማሲ ፊርጁ በጋራ መንቀሳቀስ፣ በፖለቲካ መስኩ በጋራ በትብብር ሲሰሩ የነበሩና ከእዛም ውጭ በጋራና በተናጠል በሃገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን ሲታገሉ የነበሩ ድርጅቶች በሃገሪቱ መጻኢ እጣና ወያኔን ከማስወገዱ ቀጥሎ ስለሚመጣው የስራ ምእራፍ የሚመክሩበት አጠቃላይ ሸንጎ መጥራት፣ የዚህ ምእራፍ ተግባራት ይሆናሉ።

## ወያኔ/ኢ.ህአዴግን የማስወገዱ ሂደት፤ ሁለተኛው ምእራፍ

ከትብብር ወደ አጠቃላይ ሽንጎ፣ ከሽንጎ ወደ ሽግግር መንግስት

- የተለያዩ ሃይሎች በመተባበር የሚያደርጉት ትግል በሚፈጥረው አመቺ ሁኔታ የሚጠራው አጠቃላይ ሽንጎ አንድ መሰረታዊ ተግባር ይኖረዋል። ይህም ተግባር የተወሰነ የግዜ ገደብ የተቀመጠለት፣ ስልጣኑ ጊዜያዊ የሆነ፣ አስቀድሞ የህዝብ ውክልና የሌለው መሆኑን በግልጽ ያስቀመጠ፣ የመንግስት ስልጣንን በህዝብ ለተመረጠ የፖለቲካ አካል የሚያስተላልፍ የሽግግር መንግስት ማቆም ይሆናል።

- የእዚህ የሽግግር መንግስት ዋነኛው ተግባር የፖለቲካ ስራ ይሆናል። አብይ ተግባሩ በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዳይገነባ፣ የህዝብ ውክልና ያለው መንግስት እንዳይመሰረት፣ ዜጎችን በህግ ፊት እኩል አድርጎ የሚያይ የህግ የበላይነት እንዳይሰፍን፣ ዜጎች በሃገራቸው በገዛ ህይወታቸው ላይ በነጻነት እንዳይመክሩና ፍላጎታቸውን እንዳይገልጹ ያደረጉትን፣ ወያኔ /ኢ.ህአዴግ አምባገነናዊ ፍላጎቱን ለማስፈጸም የተጠቀመባቸውን መንግስታዊ ተቋማት፤ ሁሉንም ዜጋ፣ ሁሉንም ፖለቲካዊና ፖለቲካዊ ያልሆነ ስብስብ በነጻነትና በገለልተኛነት የሚያገለግሉ ተቋማት አድርጎ ማቋቋም። እነዚህ ተቋማት በዋነኛነት፣ የሃገር መከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል፣ የዳኝነት ስርአት፣ ነጻ የመገናኛ ብዙሃን፣ ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ይሆናሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ፣ በሃገር ውስጥ የሚገኙ ህገ-መንግስታዊ ህልውና የተሰጣቸው የሙያ ማህበራት፣ የሠራተኛና የመምህራን፣ የጋዜጠኞችና እንዲሁም ሌሎች፣ በአባላቶቻቸው ነጻ ፍላጎት የሚደራጁበትና ለዴሞክራሲ ስርአት መጎልበት የራሳቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበት ሁኔታ የሚፈጠርበት ምእራፍ ይሆናል። ይህ ምእራፍ በሃገር ወስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኙ የሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ፣ ከፍተኛ  የሆነ ተሳትፎ የሚያደርጉበት፣ ለምክክርና ለስምምነት በቂ ትኩረት የሚሰጥ ሂደት ይሆናል። እነዚህን ተቋማት በስምምነት በማቆም፣ እነዚህ ነጻ ተቋማት ከተመሰረቱ በኋላ በሚደረግ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ፣ የሽግግር መንግስቱ ቦታውን በህዝብ ለተመረጠ የመጀመሪያው የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ መንግስት ያስረክባል።

## ግንቦት 7 ምን እያደረገ ነው?

ግንቦት 7 በቅድሚያ የተንቀሳቀሰው ሁሉም ተግባራቱ በበቂ እውቀትና መረጃ ላይ የተመሰረቱ መሆን ይገባቸዋል ብሎ በማሰብ  ነው። በመሆኑም፤

- ሃገራችን የምትገኝበትን አጠቃላይ ሁኔታ፣ በተለይ በእዚህ አሳሳቢና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወያኔ የሚጫወተውን ሚና በዝርዝር አጥንቷል። በእዚህ ጥናት ከደረሰበት የወያኔ/ኢ.ህአዴግ ባህርያት በመነሳት ከእዚህ ሃይል ጋር የሚደረግ ትግል ምን አይነት የትግል ስልትና ስትራተጂ፣ ምን አይነት የአደረጃጀት ዘዴዎች፣ ምን አይነት የፕሮፓጋንዳና የዲፕሎማሲ ስራ አቅጣጫዎች  ያስፈልጉታል የሚሉ ጥያቄዎች በማንሳት ምላሽ ሰጥቷል። ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ለመስራት ስለሚያስፈልጉ አስተባባሪ አጀንዳዎችና የንቅናቄው መነሻና መድረሻ ምን ይሆናል የሚለውን መርሃ ግብሩን አስቀድሞ በሚገባ አዘጋጅቶ ተንቀሳቅሷል።

- ግንቦት 7 የደረሰበትን የሁኔታዎች ግምገማ፣ የሚከተለውን የትግል ስልት፣ ለማምጣት የሚፈልገው ለውጥ ምን እንደሆነ ለማሳወቅ በሃገር ቤትና በውጭ ሃገራት ሁኔታው እንደፈቀደው በተለያዩ ስብሰባዎች፣ ጽሁፎችና የሚድያ አውታሮች አማካይነት ገለጻ አድርጓል።፡ ህዝብ ዝም ብሎ እንዲደግፈን ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚደግፈን ማዋቁ ለንቅናቄውም ሆነ ለህዝቡ ይጠቅማል ብለን ስለምናምን፣  ሁኔታው በፈቀደልን ደረጃ በቂ ጊዜ ወስደን በንቅናቄው አላማዎች ዙሪያ ሰፊ ገለጻ አድርገናል፡፡

- ንቅናቄው በየትኛውም የስራ ዘርፍ ወያኔ ካሰማራቸው ሙያተኞች የበለጠ ልምድና እውቀት ያላቸውን ግለሰቦች በማሰባሰብ የወያኔን የዲፕሎማሲ የስለላና የአፈና አቅም ሰብሮ ካሰብነው ግብ ለመድረስ የሚያስችል የእውቀትና የሙያ መሰረት ጥለናል።

- ንቅናቄው ያስቀመጠውን የትግል ስልት በስራ ላይ ማዋል የሚያስችለውን ድርጅታዊ አቅም ደረጃ በደረጃ በሀገር ውስጥና ከሃገር ውጭ በመገንባት ላይ ይገኛል።

- የሃገራችን ህዝብ በተለይ በሚድያ በኩል ያለበትን አፈና በመረዳት፣ የንቅናቄውን አላማና ራእይ ለህዝብ የምናስተዋውቅበትን፣ ውሎ አድሮም የህዝብ ትግል በሃገር አቀፍ ደረጃ በማስተባበር ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችሉ የንቅናቄው የራድዮና የጋዜጣ ስርጭት ጀምረናል።




- በትብብር መልኩ ንቅናቄው ያሰመረባቸውን የመተባበሪያ ነጥቦችና መርሆዎች ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆኑ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የጀመርነው ስራ በቅርብ ግዜ ፍሬ እንደሚያፈራና ውጤቱ ለህዝብ የሚገለጽበት ቀን መቃረቡን እናውቃለን።

- የወያኔ/ኢህዴግ አምባገነኖች ሃገሪቱን ለመግደል፣ ህዝቡን እርስ በርሱ ለማጫረስ፣ ጥሪቱን አሟጠው ለመዝረፍ የዘረጉት መርሃ ግብር እስካሁን ካደረሰው ጥፋት በተጨማሪ ሌላ ጥፋት ከመጨመሩ በፊት በአጭሩ መቅጨት የሚያስችል ሁለ ገብ እንቅስቃሴ በአጭር ግዜ ውስጥ እውን እናደርጋለን የሚል ትልቅ እምነት አለን። የግንቦት 7 ንቅናቄ ስራ የጀመረው በቅርቡ ነው። አብዛኛውን ስራ ለመስራት የሞከረው በጥንቃቄ በሰበሰባቸው ግለሰቦችና እነዚህ ግለሰቦች በገንዘባቸው፣ በግዚያቸውና በእውቀታቸው በቅድሚያ በከፈሉት አስተዋጽኦ ላይ ብቻ ተመስርቶ ነው። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከተለያዩ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የምናገኘው ድጋፍ እየጨመረ ቢመጣም ወያኔ/ኢህአዴግን የሚያክል በገንዘብና በመሳሪያ ከተደራጀ ሃይል ጋር ለሚደረገው መራራ ትግል በቂ አይደለም።

# ከእርስዎስ ምን ይጠበቃል?

በቅድሚያ ይህ ትግል የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ሃገር የማዳን የአርበኝነት ትግልም መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሁላችንም ያቅማችንን ለማበርከት የዜግነትና የሞራል ግዴታ እንዳለብን መገንዘብን ይጠይቃል።

- ግንቦት 7 ንቅናቄ በሃገራችን ምድር ወያኔ/ኢ.ህአዴግን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ የወያኔ/ኢ.ህአዴግ መሪዎችን የመሰሉ ዘረኛ ዘራፊ አምባገኖነች የመንግስት ስልጣን የማይዙበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርብናል ብሎ ያምናል። ፈሪሃ-ህዝብ የሚሰማው መንግስት በሃገር ላይ እንዲመሰረት በማድረግ፣ በሃገርና በወገን ላይ የሚሰራውን ግፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስቆም እንችላለን ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። እርስዎስ?

- ክፉ ዘመን መጥቷል። ኢትዮጵያችን ከዜጎቿ መሃል ማን እንደ ቀደምቶች ልጆቿ ለክብሯ፣ ለነጻነቷ፣ ለህልውናዋ እንደሚቆሙላት ለማወቅ የታሪክ መዝገቧን ይዛ ቆማለች። ገሚሱ ህይወቱን ለመስጠት ተሰልፏል። ገሚሱ እውቀቱን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን ማበርከት ጀምሯል፤ እርስዎስ? ምን ማድርግ እችላለሁ የሚሉ ከሆነ፣ መልሱ እነሆ፤
    - አባል በመሆን ወርሃዊ መዋጮ በማዋጣትና በሳምንት የተወሰኑ ሰአታት ለደርጅቱ ስራ በማዋል፤
    - ሙያዊና እውቀትዎን በመጠቀም በሃገራችን ዴሞክራሲ ለማስፈን የሚደረገው ትግል ማገዝ፤ የተለያዩ የጥናትና የምርምር ጠቃሚ ሰነዶችን በማዘጋጀት፣ በህዝብ ግንኙነትና በሌሎችም የስራ መስኮች በመሳተፍ፤
    - ንቅናቄው የገንዘብና የቁሳቁስ አቅሙ እንዲደራጅ፣ የጠላትን ሃይል ለማዳከም የሚጠቅሙ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለንቅናቄው በማድረስ፤
    - ንቅናቄው ጠንካራ የገንዘብ መሰረት እንዲኖረው ዳጎስ ያለ የአንድ ግዜ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ግንቦት 7ን መገደፍ ይችላሉ። ይተባበሩን፣ በጋራ ሆነን የሃገራችንን የጭንቅ ቀን ጥሪ እንመልስ እንልዎታለን።

- ብዛታችን፣ የትግላችን ፍትሃዊነትና የአላማችን ርቱእነት፣ የአሸናፊነታችንን አይቀሬነት አስቀድሞ የተነበየው ነውና እንደ ቀደምቶቻችን ሃገራችንን በመታደግ ለልጅ ልጆቻችንና ለትውልድ የሚተላለፍ አኩሪ ታሪክ በጋራ እንስራ።

## ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !

